፭ኛ ዓመት ቁጥር 4
5th Year No. 4

ባህር ዳር ታህሳስ 5 ቀን 1996 ዓ/ም
Bahir Dar, December 15, 2003

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ህግ

ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State
in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

ፖ.ሳ.ቁ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 4.00
Unit price 4.00

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 93/1996 ዓ.ም.
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ለማቋቋም አዋጅ

Contents

Proclamation No.93/2003
The Amhara National Regional State Ethics and Anti-Corruption Commission Establishment Proclamation.

አዋጅ ቁጥር 93/1996 ዓ.ም.

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽንን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና የክልሉ ነዋሪዎች የሥነ-ምግባር ብልሹነትና ሙስና የክልሉን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዕድገት የሚያግድ ተግባር መሆኑን በመገንዘባቸው፤

የክልሉን የልማት እና የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ለማፋጠንና ቀጣይነት ያለው እንዲሆን ለማድረግ ሙስናንና ብልሹ አሠራርን መከላከል እና በቁጥጥር ሥር ማዋል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ሙስናንና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል ይቻል ዘንድ ይህንኑ ለመመርመር፣ አጣርቶ ለፍርድ ለማቅረብ፣ ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲሁም በህብረተሰቡ ውስጥ መልካም ሥነ-ምግባር ይሰፋ ዘንድ ሙስናን እና ብልሹ አሠራርን መዋጋት የሚችል ነፃና እራሱን የቻለ ክልላዊ ተቋም ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

Proclamation No. 93/2003

A Proclamation Issued to Establish the Amhara National Regional State Ethics and Anti-Crruption Commission.

WHEREAS, the Amhara National Regional State and residents of the Region cognize that corruption and impropriety are hindrance for social, economic and political development of the Region;

WHEREAS, it is found necessary to prevent and bring under control corruption and impropriety in order to expedite as well as make sustainable the building of the development and democratization process of the Region;

WHEREAS, it is found necessary to establish free and independent Regional institution which is capable of investigating, prosecuting for trial, preventing and checking corruption and impropriety through the promotion of ethical values in the society;

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ ሥር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል::

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 93/1996 ዓ/ም» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ ባስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

1. «መንግስት» ማለት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ነው::

2. «የመንግስት መ/ቤት» ማለት በክልሉ መንግስት በጀት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የሚተዳደር እና የክልሉ መንግስት ሥራዎች የሚከናወኑበት ማንኛውም መ/ቤት ነው፤

3. «የመንግስት ልማት ድርጅት» ማለት በክልሉ መንግስት ባለቤትነት የሚተዳደር ወይም የጥቅም ድርሻ በሙሉ ወይም በከፊል ያለበት የልማት ድርጅት ወይም የአክሲዮን ማህበር ነው::

4. «ባለስልጣን» ማለት በክልሉ መንግስት መ/ቤት ወይም በመንግስት ልማት ድርጅት ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ በኃላፊነት እንዲያገለግል የተሾመ፣ የተመደበ፣ የተቀጠረ ወይም በሕዝብ የተመረጠ ማናቸውም ሰው ነው::

5. «የመንግስት ሠራተኛ» ማለት በክልሉ ሲቪል ሠርቪስ ሕግ ወይም በአሠሪና ሠራተኛ ሕግ ወይም ራሱን በቻለ ሌላ ሕግ የሚተዳደር እና በክልሉ መንግስት መ/ቤት ወይም በክልሉ መንግስት ልማት ድርጅት ወይም መንግስታዊ ባልሆነ ድርጅት ውስጥ ተሹሞ ወይም ተመድቦ ወይም ተቀጥሮ የሚሠራ ማናቸውም ሰው ነው::

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Region, in accordance with the power vested in it under Article 49 sub-Article 3/1/ of the Revised Constitution of the Region, hereby issues this proclamation.

PART ONE
GENERAL PROVISIONS

1. Short Title

This Proclamation may be cited as " The Amhara National Regional State Ethics and Anti-Corruption Commission Establishment Proclamation No. 93/2003."

2. Definitions

In this proclamation, unless the context requires other wise:

1. "Government" means the Amhara National Regional State.

2. "Public Office" means any office which is fully or partially administered by the regional state budget and within which activities of the regional state are being carried out.

3. "Public Enterprise" means public enterprise or share association, which is administered, or having share benefit fully or partially by the ownership of the Regional State.

4. "Official" means any official who is appointed, assigned, employed or elected by the public to serve as a head in offices of the Regional state or in public offices or in non-governmental organizations;

5. " Public Servant" means a person who is governed by the Regional Civil Service Law or by labour law or by other autonomous law and who is appointed or assigned or employed and working in office of the Regional State or in the Regional public enterprises or in a non-governmental organization.

6. «የሥነ ምግባር አውታሮች» ማለት በመንግስት አስተዳደር ውስጥ ምግባረ ብልሹ ባህሪያትን በከፍተኛ ደረጃ ለመቀነስና ሙያዊ ብቃትን እና መልካም ሥነ-ምግባርን ለማበረታታት የሚያገለግሉ ዘዴዎች፣ አካሎች፣ ሥርዓቶች ወይም አስፈላጊ ሙያዎች እና የመሳሰሉትን የሚያጠቃልል ነው::

7. «መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት» ማለት ከመንግስት በጀት ውጭ የሚተዳደርና የአባላቱን ጥቅም ለማስከበር፣ የሌላ 3ኛ ወገን ጥቅምን ለማስጠበቅ ወይም ለተወሰነ ማህበረሰብ አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመ ማንኛውም ድርጅት/ማህበር/ነው::

8. «ሰው» ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው::

9. «የብሔረሰብ ምክር ቤት» ማለት በክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 73 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ መሠረት የተቋቋሙ የአዊ፣ የዋግ ኽምራና አሮሚያ ዞኖች የብሔረሰብ ምክር ቤቶችን የሚገልጽ ነው::

ክፍል ሁለት

ስለ ኮሚሽኑ መቋቋም፣ አላማ፣ ሥልጣን፣ አደረጃጀትና አመራር

3. ስለ መቋቋም

1. የክልሉ የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን/ከዚህ በኋላ «ኮሚሽኑ» እየተባለ የሚጠራ/ ራሱን የቻለና ህጋዊ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግስት መ/ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል::

2. የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል::

4. የኮሚሽኑ ዋና መ/ቤት

የኮሚሽኑ ዋና መ/ቤት በባህርዳር ከተማ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች የክልሉ አካባቢዎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ሊያቋቁም ይችላል::

6. "Ethics infrastructure" means mechanisms, bodies, procedures or essential skills and the like that serve to reduce substantially unethical conducts and to encourage efficiency and integrity in the public service.

7. "Non-governmental organization" means any organization/association which is financed with non-governmental budget and established to maintain the interest of its members, secure the benefits of other third parties or to render services to a certain part of a society;

8. "Person" means natural or juridical person.

9. "The Nationality Council" means referring to nationality councils of Awi, Waghimra and Oromyia zones, which are established pursuant to Article 73 sub-Article 2/a/ of the Regional constitution.

PART TWO

Establishment, Objective, Power, Organization and Leadership of the Commission.

3. Establishment

1. The Regional Ethics and Anti-corruption Commission /here in after referred to as "The Commission"/ is here by established by this proclamation as an autonomous Regional state office having legal personality.

2. The Commission shall be accountable to Head of the Government.

4. Head Office of the Commission

The Commission shall have its head office in Bahir Dar and may have offices in other areas in the Region as deemed necessary.

5. **የኮሚሽኑ አላማዎች**

ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል፡-

1. የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ትምህርትን በማስፋፋት መልካም ሥነ ምግባር ያለውና ሙስናን ሊሸከም የማይችል ሕብረተሰብ ለመፍጠር ጥረት ማድረግ፣

2. በክልሉ ውስጥ የሙስና ወንጀልንና ብልሹ አሠራርን መከላከል፣ መመርመርና ሙሰኞችን ለፍርድ አቅርቦ በማስቀጣት እንዲታረሙ ማድረግ፣

3. በክልሉ ውስጥ ሃቀኛና ታማኝ የሕዝብ አገልግሎት እንዲሰፍን ጥረት ማድረግ።

6. **የኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር**

ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት ልማት ድርጅቶች ወይም ክልል በቀል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ ከባድ የሥነ-ምግባር ጉድለት ስለመፈፀሙ ጥቆማ ሲደርሰው ወይም በቂ ጥርጣሬ ሲኖረው የማጣራት ወይም እንዲጣራ የማድረግና ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ የመከታተል፣

2. በወንጀል ሕግና በሌሎች ሕጐች ውስጥ የተመ ለከቱት የሙስና ወንጀሎች በመንግስት መሥ ሪያ ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ወይም እነዚሁ የተካፈሉበት በሆነ ጊዜ በግል ዘርፍ ስለመፈፀማቸው ጥቆማ ሲደርሰው ወይም በቂ ጥርጣሬ ሲኖረው የመመርመር፣ እንዲመረመር የማድረግ እና ክስ የመመስረት፣

3. የሙስና ወንጀሎችን በመመርመር ሂደት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርአት ሕግ መሠረት ማናቸውንም ግቢ፣ የሥራ ቦታ፣ ተሽከርካሪ ወይም ማናቸውንም ሌላ ንብረት እንደአስፈላጊነቱ የመፈተሽ፣ የመበርበር ወይም የመያዝ፣

5. **Objectives of the commission**

The Commission, pursuant to this proclamation, shall have the following objectives:

1. To strive to create an aware society having ethical values and where corruption shall not condoned by promoting ethics and anti-corruption education.

2. To prevent, investigate corruption offences and improprieties and make corrupt persons be punished and corrected by bringing them to justice in the Region.

3. To strive that genuine and honest public service prevails in the Region.

6. **Powers and Duties of the Commission**

The Commission, pursuant to this proclamation, shall have the following powers and duties:

1. Investigate or cause the investigation of any complaints of alleged or suspected serious breaches of ethics in government offices, public enterprises or regionally originated non-governmental organizations, and follow up the taking of proper measures;

2. Investigate or cause the investigation of any alleged or suspected corruption offences specified in the penal code or in other laws where they are committed in public offices, public enterprises or in non-governmental organizations, or in private sector with participation of public offices, public enterprises or non-governmental organizations; and prosecute same;

3. Inspect, search or seize, as may be necessary, any premises, working place, vehicle, or any property in accordance with the criminal procedure code during the process of investigating of offences related with corruption;

4. በወንጀልኛ መቅጫ ሥነ-ሥርአት ሕግ መሠረት በሙስና ወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎችን ከ48 ሰአት ላልበለጠ ጊዜ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ አስሮ የማቆየትና ፣ በሕግ መሠረት በዋስትና የመልቀቅ እና የተጠርጣሪዎችን የጣት አሻራና ፎቶ ግራፍ የመውሰድ፤

5. ለምርመራ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማናቸውንም ሰው በወንጀልኛ መቅጫ ሥነ-ሥርአት ሕግና በሌሎች ሕጐች መሠረት አስቀርቦ የመጠየቅ፣ ቃል የመቀበል እና ከማናቸውም ሰው ወይም መ/ቤት ማስረጃ እንዲቀርብለት የማዘዝ፤

6. ከሙስና ወንጀል ጋር የተያያዘ እና በባንክ የተቀመጠ ገንዘብ ለመኖሩ በቂ ጥርጣሬ ወይም ማስረጃ ሲኖረው በማናቸውም ባንክ የሚገኝ የተጠርጣሪዎች የባንክ ሂሳብ በኮሚሽኑ ትዕዛዝ መሠረት እንዲመረመር የማድረግ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲከበር የማድረግ፤

7. በክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በልማት ድርጅቶች ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እና አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ውስጥ ለሙስና የተጋለጡ የአሠራር ሥርአቶችን በመመርመር እንዲሻሻሉ በማድረግ ሙስናን የመከላከል፣ በሌሎች ሰዎች ሲጠየቅ ተመሳሳይ ምክርና ድጋፍ የመስጠት፤

8. የመንግስት ባለስልጣኖችን እና በህግ ሃብታቸውንና የገንዘብ ጥቅማቸውን እንዲያስመዘግቡ ግዴታ ያለባቸውን የመንግስት ሠራተኞች ሃብትና የገንዘብ ጥቅሞች መዝግቦ የመያዝ ወይም ተመዝግቦው እንዲያዙ የማድረግ፤

9. ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ በምርመራ ላይ ያሉ ሰዎች ሃብት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲይንቀሳቀስ የማድረግ፣ በሙስና ወንጀል የተገኘ መሆኑ የተረጋገጠ ማናቸውን ንብረት ወይም ሃብት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲወረስና በሃራጅ ተሽጠ ወይም ሳይሸጥ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ማድረግ፤

10. የሥነ-ምግባር ደንቦች እና የፀረ ሙስና ሕጐች መከበራቸውን የመከታተል እና የማረጋገጥ፣ ስለአፈጻፀማቸው የምክር አገልግሎት የመስጠት፤

4. Detain, with out court warrant, persons suspected of corruption offences for a period not exceeding 48 hours in accordance with criminal procedure code, release on bail pursuant to the law and take finger prints and photographs;

5. Summon, interrogate and receive the testimony of persons and order the presentation an evidence from any person or office in accordance with the criminal procedure code and other laws, where it is found necessary for investigation;

6. Investigate, with the order of the commissioner any bank account of suspected persons where there is reasonable suspicion or evidence in connection with corruption and for there is money deposited in any bank; and cause the attachment, with court order, of same where necessary;

7. Prevent corruption by examining and improving working procedures which are subject to computation offices, public enterprises or in non-governmental organizations and in service rendering institutions; and advise or assist on same, upon request, any other persons;

8. Register or cause the registration of the assets and financial interests of public officials and other public servants as specified by law;

9. Freeze, by court order, the assets of any person who may be under investigation for corruption; and cause through court order, the forfeiture of any assets and wealth obtained in connection with corruption offence to the state or dispose same by or without public auction;

10. Follow up and ensure the enforcement of codes of ethics and anti-corruption laws and give advice in the implementation of same;

11. ሥነ-ምግባርና ሙስናን በተመለከተ ጥናትና ምርምር የማድረግ፣ ተመሳሳይ ሥራዎችን የመደገፍና የኮሚሽኑን አላማዎች ለማራመድ የሚረዱ ሪፖርቶችን እና ቴክኒካዊ ጥናቶችን አሳትሞ ለህብረተሰቡ የማሰራጨት፣

11. Undertake research on ethics and corruption, give support to similar activities and publish reports and technical studies to further the objective of the commission;

12. የሥነ-ምግባር ደንቦች ሲጣሱ የሚወሰዱ እርምጃዎች ከተፈፀሙ ጥፋቶች ጋር የተጣጣሙ ወይም የተመጣጠኑ እንዲሆኑ ሌሎች የሥነ ምግባር አውታሮችን የማስተባበር፣

12. Coordinate the ethical infrastructures to ensure that ethical codes and measures are in harmony and compatible with measure to be taken against ethical breaches;

13. ስለሙስና ጉጅነት የሕዝቡ ንቃተ ሕሊና እንዲጎለብት በማስተማር እና መልካም ሥነ-ምግባር በሕዝቡ አገልግሎት እና በሕብረተሰቡ ውስጥ እንዲስፋፉ በማድረግ ሙስናን እና ብልሹ አሠራርን መዋጋት፣

13. Combat corruption and impropriety by creating awareness through educating the public about the effect of corruption and the promotion of ethics in public service and in the society;

14. የሕግ አውጭና የዳኝነት አካላቱን ሳይጨምር ለመንግስት መስሪያ ቤቶችና ለመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚያገለግሉ የሥነ-ምግባር ደንቦች ማዘጋጀት፣ መዘጋጀታቸውን የማረጋገጥ እና አፈፃፀማቸውን የመከታተል፣ ከሕግ አውጭና ከዳኝነት አካላት ጥያቄ ሲቀርብለት በስነ ምግባር ደንብ አዘገጃጀት ረገድ ምክር የመስጠት፣

14. Apart from legislative and judicial bodies, prepare codes of ethics for government offices and public enterprise, ensure the preparation of same and follow up their implementation; provide, upon request, advice to legislative and judicial bodies in preparing codes of ethics;

15. ለጠቋሚዎች እና ለምስክሮች የአካልና የሥራ ዋስትና ጥበቃ የመስጠት፣

15. Provide physical and job security protection to whistle blowers and witnesses;

16. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 መሠረት ቅርጫፍ ጽ/ቤቶችን ካቋቋመ የሥራ ዝርዝራቸውን የማዘጋጀት እና አፈፃፀማቸውን የመከታተል፣

16. Prepare lists of job description and follow up their implementations if it establishes branch offices pursuant to article 4 of this proclamation;

17. ሙስናን በመታገልና በመከላከል ረገድ ውጤት ያስገኙ ሰዎችን እና መስሪያ ቤቶችን አወዳድሮ ለሽልማት የሚበቁበትን ሥርአትና መለኪያ በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ፣

17. Establish and implement procedures and standards for the selection of awards, upon competition of persons or offices who are successful in fighting and preventing corruption;

18. ተመሳሳይ አላማዎች ካሏቸው ክልላዊና ሃገራዊ አካላት ጋር ግንኙነት የመፍጠርና ትብብር የማድረግ፣

18. Liaise and cooperate with regional and national bodies with similar objectives;

19. የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ውል የመዋዋልና በራሱ ስም የመክሰስም ሆነ የመከሰስ፣

19. Own property, enter into contract, sue and be sued in its own name;

20. ከፍ ብሎ ከተዘረዘሩት ኃላፊነቶቹ መካከል የመመርመርና የመክሰስ ሥልጣኑን እንደአስፈላጊነቱ ለክልሉ ፖሊስና የአቃቤ ሕግ አካላት በውክልና የመስጠትና የማሰራት፣

20. Delegate to exercise its power to investigate and charge, among the responsibilities specified herein above, to the regional police and prosecuting bodies as deemed necessary;

21. በሕግ የሚሰጡትንና አላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱትን ሌሎች ተግባራት የማከናወን::

7. ስለኮሚሽኑ የአሠራር ነፃነት

የዚህ አዋጅ አንጽ 3 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ቢኖርም ኮሚሽኑ ሥራውን በማከናወን ረገድ ከማናቸውም ሰው ጣልቃ ገብነት ወይም አመራር ነጻ ነው::

8. ድርጅታዊ አቋም

ኮሚሽኑ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል:-

1. በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሾሙ ኮሚሽነር እና ምክትል ኮሚሽነር፤
2. አማካሪ ቦርድ፤
3. ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ሠራተኞች::

9. የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር

1. ተጠሪነቱ ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ሆኖ ኮሚሽነሩ የኮሚሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የኮሚሽኑን ሥራዎች ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል::

2. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ አንድ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ:-

ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 የተዘረዘሩትን የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ. የክልሉን ሲቪል ሰርቪስ ሕግ አጠቃላይ መርሆዎች መነሻ አድርጐ በሚወጣው መመሪያ መሠረት የኮሚሽኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

ሐ. የኮሚሽኑን አመታዊ የሥራ ፕሮግራምና የ5 አመት በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ. ኮሚሽኑ በተፈቀደለት በጀትና ፕሮግራም መሠረት የፋይናንስ ሕግን ተከትሎ ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፤

21. Perform such other duties as may be defined by law and under take other activities necessary for the attainment of its objectives.

7. Operational Indepence of the Commission

Notwithstanding to the provision of sub-Article 2 of Article 3 of this proclamation, the Commission shall be free from any intervention or direction by any person with regard to the conduct of its operation.

8. Organization

The Commission shall have the following bodies:

1. A Commissioner and a vice-Commissioner appointed by Head of the Government;
2. An Advisory Board;
3. Such other officers as may be necessary.

9. Powers and Duties of the Commissioner

1. The Commissioner being accountable to head of the Regional Government, shall be the chief executive of the Commission and shall organize, direct and administer the activities of the Commission.

2. Without prejudice to sub-Article 1 of this Article, the Commissioner shall:

a. Exercise the powers and duties of the Commission specified under Article 6 of this proclamation;

b. Employ, administer and dismiss employees of the Commission in accordance with directive to be issued based on the general principles of the Regional Civil Service Law;

c. Prepare the annual work program and the five-year budget of the commission and implement same up on approval;

d. Effect expenditure based on the approved budget and program of the commission in accordance with financial laws.

ሠ. የኮሚሽኑ ባለሙያዎችና ሠራተኞች በሙስና ወንጀል የተጠረጠሩትን በሕግ መሠረት ለመመርመር ወይም ለማሰር እንዲችሉ ሥልጣን ይሠጣል፤

ረ. ምርመራው በመከናወን ላይ ላለ ጉዳይ አግባባነት ያለው በሆነ ጊዜ የማንኛውም ሰው የባንክ ሂሣብ እንዲፈተሽ እና አስፈላጊ መረጃ እንዲሰበሰብ ትዕዛዝ ለመስጠት ይችላል፤

ሰ. የኮሚሽኑ ጠቅላላ የአሠራር ሂደት የሥራ ግምገማ ውጤትና አስተያየት አስመልክቶ ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ሪፖርት ያቀርባል፤

ሸ. ከሦሥተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ኮሚሽኑን ይወክላል።

3. ኮሚሽነሩ ለኮሚሽኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኮሚሽኑ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

10. <u>የኮሚሽነሩ የአገልግሎት ዘመንና ከሥራ መነሳት</u>

1. የኮሚሽነሩ የአገልግሎት ዘመን ስድስት አመት ይሆናል፤ ሆኖም ርዕሰ መስተዳድሩ ሲያምንበት በድጋሚ ሊሾም ይችላል።

2. ኮሚሽነሩ የአገልግሎት ዘመኑ ከማለቁ በፊት ከዚህ በታች በተመለከቱት ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር ከሥራው አይነሳም:-

ሀ. በወንጀል ተከሶ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ጥፋተኛ መሆኑ ሲረጋገጥና ይህም በሥራው ለመቀጠል የማያስችለው መሆኑ በሚሚው አካል ሲታመንበት፤

ለ. በአዕምሮ ወይም በአካል ህመም ምክንያት ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን ሲሳነው፤

ሐ. ዝርዝሩ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ ሥራውን በሚገባ መወጣት አለመቻሉ ሲታመንበት፤

መ. እራሱ የመልቀቂያ ጥያቄ ሲያቀርብ።

f. Authorize, in accordance with the law, experts and employees of the Commission to carry out investigation or to arrest persons who are suspected of corruption;

g. Issue warrants of searching and obtaining information when there is reasonable suspicion that such is relevant to a case under investigation;

h. Submit report to Head of the Regional Government concerning the outcome and recommendation of the entire performance process ot the Commission;

i. Represent the Commission in its all relations with third parties.

3. The Commissioner may delegate part of his powers and duties to other officials and employees of the commission to the extent necessary for the effectiveness and efficiency of the Commission.

10. <u>Term of Service and Removal From Office of the Commissioner</u>

1. The term of service of the Commissioner shall be six years; he may, however, be reappointed upon the conviction of Head of the Regional Government.

2. The Commissioner shall not be removed from his office before his term of service, unless reasons specified herein under other wise:

a. When he is charged and found guilty of an offence by the court of law and such offence is believed by the authorizing body that it does not allow him to stay on his job;

b. When he can no longer carry out his responsibilities on account of mental or physical illness;

c. When it is believed that he is unable to discharge his task properly, and for which particulars shall be determined by directive;

d. When he submits a request for resignation.

11. የምክትል ኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባር

ምክትል ኮሚሽነሩ ተጠሪነቱ ለኮሚሽነሩ ሆኖ፡-

1. ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ኮሚሽነሩን ተክቶ ይሠራል፤

2. በኮሚሽኑ ሥር የተዋቀሩትን አደረጃጀቶችና የሥራ ክፍሎች ከኮሚሽነሩ በሚሰጠው መመሪያ እና በኮሚሽኑ የአሠራር ደንብ መሠረት ይመራል፣ ያስተባብራል።

12. የምክትል ኮሚሽነሩ የአገልግሎት ዘመንና ከሥራ መነሳት

የምክትል ኮሚሽነሩን የሥራ ዘመንና ከሥራ መነሳት አስመልክቶ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ኮሚሽነሩን አስመልክቶ የተደነገገው ተፈፃሚ ይሆናል።

13. ስለኮሚሽኑ ሠራተኞች ቅጥር ሁኔታ

1. ኮሚሽነሩ በዚህ አዋጅ ለኮሚሽኑ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ለማከናወን በሚያስፈልግ መጠን ችሎታን እና መልካም ሥነ-ምግባርን መሠረት አድርጉ ሠራተኞችን ይቀጥራል።

2. ኮሚሽነሩ ከአማካሪው ቦርድ ጋር በመመካከር የክልሉን ሲቪል ሠርቪስ ሕግ አጠቃላይ መርሆዎች መሠረት በማድረግ የኮሚሽኑን የሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብና መመሪያ አዘጋጅቶ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሲፀድቅ በሥራ ላይ ያውላል፣ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረትም ከሥራ ያሰናብታል።

14. ስለ አማካሪ ቦርድ መቋቋም

1. የሚከተሉት አባላት የሚኖሩትና/ከዚህ በኋላ «ቦርዱ» እየተባለ የሚጠራ/ አንድ የኮሚሽኑ አማካሪ ቦርድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡-

ሀ. በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሰየም-------ሰብሳቢ

ለ. ኮሚሽነሩ---------- አባል

ሐ. የሙስና ወንጀል መከላከል፣ ምርመራና ክስ ማደራጃ መምሪያ ኃላፊ---------- አባልና ፀሐፊ

11. Powers and Duties of the Vice Commissioner

The Vice Commissioner, being accountable to the Commissioner, shall:

1. Act on behalf of the commissioner in his absence or under circumstance when he is unable to perform his normal duties;

2. Direct and coordinate the organizations and sections structured under the commission by the directive entrusted to him by the commissioner and in accordance with working procedure of the Commission.

12. Term of Service and Removal from Service of the Vice-Commissioner

The provision stipulated in Article 10 of this proclamation concerning term of service and removal from service of the Commissioner shall be also applicable to the Vice-Commissioner.

13. Recruitment of Employees of the Commission

1. The Commissioner may recruit such employees, on merit and integrity, to the extent required necessary for the performance of powers and duties of the Commission under this proclamation.

2. The Commissioner shall, with the advice of the Advisory Board, put in effect following the general principles of the Regional Civil Service Law, the terms and conditions of recruitment of employees subject to the approval of the Council of the Regional Government; dismiss employees in accordance with the Administrative Regulation.

14. Establishment of the Advisory Board

1. There shall be established an Advisory Board to the Commission /herein after referred to as "The Board"/ the member of which are the following:

a. One who is designated by Head of Government ----------chairperson

b. The Commissioner----------member.

c. Department Head of Prevention, Investigation and Charging Files of Corruption Offences------ member and secretary

መ. የሥነ-ምግባር ትምህርት፣ ሥልጠናና የሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት ኃላፊ---- አባል

ሠ. የአቅም ግንባታ ቢሮ ኃላፊ---------- አባል

ረ. የፍትህ ቢሮ ኃላፊ---------- አባል

ሰ. የአስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ቢሮ ኃላፊ---አባል

ሸ. የክልሉ ዋና አዲተር---------- አባል

ቀ. በደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለስልጣን የክልሉ ተጠሪ---------- አባል

በ. በክልሉ ምክር ቤት እና በብሔረሰብ ምክር ቤቶች አፈ-ጉባኤዎች የሚመረጡና የየምክር ቤቶቹን ድጋፍ ያገኙ አንድ የክልል ምክር ቤት አባልና አንዳንድ የየብሄረሰብ ምክር ቤቶች ተወካዮች-------አባላት

ተ. በክልሉ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አንድ ተወካይ----------አባል

ቸ. በክልሉ ውስጥ የተደራጀው የንግዱ ህብረተሰብ አንድ ተወካይ---------- አባል

ኀ. የብዙሃን መገናኛ ድርጅት አንድ ተወካይ-----አባል

ኘ. የሃይማኖት ተቋማት ሁለት ተወካዮች---አባላት

ኀ. በኮሚሽነሩ የሚመረጡ ሁለት ተወካዮች----------አባለት::

2. የቦርዱ ተጠሪነት ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል::

15. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. ሙስናን እና ብልሹ አሠራርን በመዋጋት ረገድ የቅድሚያ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ተግባራትን በመለየትና የሥነ-ምግባር ትምህርትን በማስፋፋት ረገድ ኮሚሽነሩን ማማከር፤

d. Ethics Education, Training and Public Relation, Head----------member

e. Capacity Building Bureau, Head--- ------member

f. Justice Bureau, Head---------- ----------member

g. Administration and Security Affairs Bureau, Head----------member

h. Auditor General of the Region----------member

i. The Regional Agent for Security Immigration and Refugee Affairs Authority----------member

j. Council members, one from the Regional Council, and one reprsentative from each Nationality Council, nominated by the respective speakers and approved by the respective councils---------- members.

k. One representative from non governmental organizations working in the Region.----member.

l. One representative from the organized business community in the Region----------member.

m. One representative from the mass media Agency ----------member

n. Two representatives from religious institutions----------members

o. Two representatives nominated by the Commissioner----------members.

2. The Board shall be accountable to the Council of the Regional Government.

15. <u>Powers and Duties of the Board</u>

The Board shall have the following powers and duties:

1. Advise the Commissioner on the priority of the measures to be taken to combat corruption and other unethical practices and to promote ethics education;

2. የኮሚሽኑን የአሠራር፣ የሠራተኞች አቀጣጠርና አስተዳደራዊ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች የማጥናትና ስለሚሻሻሉበት ሁኔታ ኮሚሽኑን የማማከር፤

2. Study the operational, employment and administrative policies and strategies of the commission, and advise the commissioner on how to improve them;

3. በኮሚሽኑ ሠራተኞች ላይ በሚቀርቡ አቤቱታዎች ላይ የተወሰዱ የዲሲፕሊን እርምጃዎችን በሚመለከት በየጊዜው በኮሚሽኑ የሚቀርቡትን ሪፖርቶች ተቀብሎ አስፈላጊውን ምክር የመስጠት፤

3. Receive and consider reports from the commissioner on complaints and disciplinary measures taken against employees officers of the commission and to give the necessary advice to the commissioner;

4. በምርመራ ላይ ያለ ሰው ወይም ድርጅት የባንክ ሂሳብ እንዲፈተሽ ወይም መረጃ እንዲሰበሰብ በኮሚሽኑ የተሰጡ ትእዛዞችን ተገቢነት በሚመለከት በየጊዜው ከኮሚሽኑ ሪፖርት የመቀበልና አስፈላጊ የመሰለውን ምክር የመስጠት፤

4. Receive periodic reports from the commissioner justifying the issuance of warrants to search or obtain information on bank accounts held by any person or organization under investigation and to give the necessary advice as it deems necessary;

5. የቦርዱን ሥራ ለማከናወን አስፈላጊ የሆኑ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን ከአባላቱ መካከል የማቋቋምና ከእነዚሁ ኮሚቴዎች በየጊዜው ሪፖርት እንዲቀርብለት የማድረግ፤

5. Establish various committees from among its members as it may deem necessary for the effective and efficient performance of its functions and receive periodic reports from such committees;

6. ለሥራ አስፈላጊ የሆኑ ባለሙያዎችን በአስረጂነት የመጥራት፤

6. Call experts as resource person necessary for its activities;

7. ሙስናን በመታገል እና በመከላከል ጥሩ ውጤት ያስገኙ ግለሰቦችን እና መሥሪያ ቤቶችን አስቀርቦ በውድድር ስለሚሸለሙበት ሁኔታ ኮሚሽኑን ማማከር፤

7. Advise the commission on the selection and awarding upon competition, of persons or offices who are successful in fighting and preventing corruption;

8. ስለ ሥራው እንቅስቃሴ በተለይም ለኮሚሽኑ የተሰጡ ማናቸውንም ምክሮች የሚያሳይና የተሠሩ ሥራዎችን የሚገልጽ ጠቅለል ያለ መግለጫን የያዘ፣ ችግሮችን ለይቶ የሚያመለክትና ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች የሚጠቁም ሪፖርት በየስድስት ወሩ ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የማቅረብ፤

8. Submit report, every six month, to head of the regional government which should outline in particular any advice given to the Commissioner a summary of its activities, and highlight problem areas with suggestions on how to resolve them;

9. ከኮሚሽኑ የሚሠሩትን ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራት የማከናወን::

9. Perform such other similar activities assigned to it by the Commissioner.

16. <u>የቦርዱ የስብሰባ ሥርዓት</u>

16. <u>Meeting Procedure of the Board</u>

1. ቦርዱ በየሦስት ወሩ አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ኮሚሽኑ ከሰብሳቢው ጋር በመመካከር በማናቸውም ጊዜ ስብሰባ እንዲጠራ ሊያደርግ ይችላል፤

1. The Board shall hold a regular meeting once every three month; provided, however, the chairperson of the Board may on his own initiative or upon the request of the commissioner, at any time, call extra ordinary meeting as may be necessary.

2. ከቦርዱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ በስብሰባው ከተገኙ ምልአተ-ጉባዔ ይሆናል።

3. የቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፣ ሆኖም ድምፁ እኩል በተከፈለ ጊዜ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

ክፍል ሦስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

17. በጀት

የክልሉ መንግሥት የኮሚሽኑን የአምስት ዓመት በጀት ይመድባል፣ ይኸውም እንደገና በኮሚሽኑ ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ መሠረት ተዘርዝሮ የሚቀርብና የሚፈቀድ ይሆናል።

18. የሂሣብ መዛግብት

1. ኮሚሽኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።

2. የኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና አዲተር መ/ቤት በየጊዜው ይመረመራሉ።

19. ስለ ኮሚሽኑ የፖሊስነትና የዐቃቤ ሕግነት ሥልጣን

ስለመመርመርና ስለመክሰስ በሃገሪቱ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግና በሌሎች ሕጐች ለፖሊስና ለዐቃቤ ሕግ የተሰጠ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ውስጥ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ለኮሚሽኑ ተሰጥቷል።

20. ተፈፃሚነት ስላላቸው ሕጐች

የሙስና ወንጀሎችን ለመዳኘት በፌዴራሉ መንግስት የወጣውና በሥራ ላይ ያለው የፀረ ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/1993 ዓ/ም /እንደተሻሻለ/ በብሔራዊ ክልሉ ውስጥ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

2. There shall be a quorum where more than half of the members are present.

3. Decisions of the Board shall be passed by majority vote; in case of a tie, the chairperson shall have casting vote.

4. Without prejudice to the provisions of this Article, the Board may issue its own rules of procedures.

PART THREE
Miscellaneous Provisions

17. Budget

The Regional Government shall allocate the five years budget of the Commission, which shall further be apportioned and approved in accordance with the annual work plan of the Commission.

18. Books of Accounts

1. The Commission shall keep complete and accurate books of accounts.

2. Books of accounts and financial as well as property related documents of the Commsion shall be frequently Audited by the office of the Regional Auditer-General.

19. The police and Prosecution Power of the Commission.

The investigation and prosecution powers of the police and public prosecutor specified under the criminal procedure code of the the country and other laws are hereby rested in the Commission with regard to matters covered in this proclamation.

20. Applicable Laws

The Anti-corruption special procedure and evidence law proclamation (as amended) No. 236/2001, which is issued by the Federal Government to judge offences of corruption and which is in effect, shall be applicable in the national Region.

21. የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች

1. በየደረጃው በሚገኙ የመንግስት መ/ቤቶች ወይም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ውስጥ የሥነ-ምግባር ሁኔታን የሚያስተባብሩ እና የየመስሪያቤቶችን ወይም የመንግስት ልማት ድርጅቶችን የበላይ ኃላፊዎች የሚያማክሩ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ይቋቋማሉ::

2. እያንዳንዱ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ተጠሪነቱ ለመሥሪያ ቤቱ ሆኖ ከኮሚሽኑ ጋር የሥራ ትብብር ይኖረዋል::

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ እና ሁለት የተደነገገው ቢኖርም ኮሚሽኑ በክልሉ የመንግስት መ/ቤቶች ወይም በክልሉ የመንግስት የልማት ድርጅት ውስጥ ከሥራው ጋር ተዛማጅነት ያለው አካል መኖሩን ሲያምንበት እንደ አስፈላጊነቱ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል አድርጉ ሊጠቀምበት ይችላል::

22. የመተባበር ግዴታ

ማናቸውም ሰው ከኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር ጋር በተያያዘ ለሚጠየቀው ትብብርና ድጋፍ የመተባበር ግዴታ አለበት::

23. ቅጣት

በሌላ ሕግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር:-

1. ማንም ሰው ለኮሚሽኑ መረጃ ወይም ማስረጃ በሰጠ ሰው ላይ ተጽዕኖ ለማድረግ ወይም ጉዳት ለማድረስ የሞከረ ወይም ያደረሰ ወይም ይህንኑ ሰው ለመቅጣት የሞከረ ወይም የቀጣ እንደሆነ ከሦስት ዓመት በማያንስ ከአሥራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከስድስት ሺህ ብር በማያንስ ከሃያ አምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

2. ማንኛውም የኮሚሽኑ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ በሕግ የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ ከዚህ የተነሳ ያገኘው ጥቅም መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከአምስት ዓመት በማያንስ ከአሥራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና ከሦስት ሺ ብር በማያንስ ከአሥር ሺ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

21. Ethics Liaison Units

1. There shall be established Ethics Liaison Units at every level of the public offices and public enterprises the duty of which shall be to coordinate ethical issues or public enterprises.

2. The liaison unit shall be accountable to the office and it may cooperate with the Commission concerning its activities.

3. Notwithstanding to the provisions of sub-Article 1 and 2 of this Article, the Commission presuming that there is a body relevant to its activity in the regional public offices or enterprises may use this body as Ethics Liaison units as deemed necessary.

22. Duty to cooperate

Any person is duty bound to cooperate whenever the commission in connection with its powers and duties requires cooperation and assistance.

23. Penalty

Unless it is punishable with more severe penalty under other laws:

1. Whosoever attempts to influence harm or punish or who influences harms or punishes any person who gives evidence or provides information relating to corruption offences to the commission shall be punishable with rigorous imprisonment not less than three years and not exceeding fifteen years; and with fine not less than Birr six thousand and not exceeding Birr twenty five thousand.

2. Any official or staff of the commission who abuses the powers and responsibilities legally entrusted to him shall, there from, be punishable with rigorous imprisonment not less than five years and not exceeding fifteen years; and with fine not less than Birr three thousand and not exceeding Birr ten thousand.

3. ማንም ሰው ሆነ ብሎ ኮሚሽኑን ለማሳሳት ወይም ሌላውን ሰው ለመጉዳት ሃሰተኛ ሪፖርት ወይም መረጃ ለኮሚሽኑ ያቀረበ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማያንስ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከሦስት ሺ ብር በማያንስ ከአሥር ሺ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

4. ማንም ሰው የኮሚሽኑ ሠራተኛ መስሎ በመቅረብ የማታለል ሥራ የፈፀመ እንደሆነ ከሁለት ዓመት በማያንስ ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከአምስት ሺ ብር በማያንስ ከአሥራ አምስት ሺ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

5. ማንም ሰው በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 22 በተደነገገው መሠረት ኮሚሽኑን ለመተባበር እንቢተኛ የሆነ እንደሆነ ከስድስት ወር በማያንስ ከአራት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት እና ከአንድ ሺህ ብር በማያንስ ከአምስት ሺ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

6. ማንም ሰው የኮሚሽኑን ሥራ ያደናቀፈ ወይም ለማደናቀፍ የሞከረ እንደሆነ ከሁለት ዓመት በማያንስ ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከአምስት ሺ ብር በማያንስ ከሃያ ሺ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል:: ወንጀሉ የተፈጸመው ኃይል በመጠቀም የሆነ እንደሆነ ቅጣቱ በዚህ ንዑስ አንቀጽ የተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት ይሆናል::

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1፣ 3፣ 4፣ 5ና6 የተመለከቱት ወንጀሎች የሕግ ሰውነት ባለው ድርጅት በተፈጸሙ ጊዜ መቀጮው አምስት እጥፍ ይሆናል::

24. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1. ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ተፈጽመው ምርመራቸው በጅምር ወይም በሂደት ላይ ያሉትም ሆነ የተጠናቀቁ ወይም በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ያሉ የሙስናና ከሙስና ጋር የተያያዙ የወንጀል ጉዳዮች በነበሩበት ሁኔታ ቀጥለው ውሳኔ ያገኛሉ::

3. Whosoever with the intent to mislead the commission or to injure others submits a false report or evidence to the commission shall be punishable with rigorous imprisonment not less than one year and not exceeding five years; and with fine not less than Birr three thousand and not exceeding Birr ten thousand.

4. Whosoever commits a deceitful act by pretending to be the staff of the commission shall be punishable with rigorous imprisonment not less than two years and not exceeding seven years and with fine not less than Birr five thousand and not exceeding Birr fifteen thousand.

5. Whosoever refuses to cooperate with the commission as provided for in Article 22 of this proclamation shall be punishable with simple imprisonment not less than six months and not exceeding four years; and with fine not less than Birr one thousand and not exceeding Birr five thousand.

6. Whosoever obstructs or attempts to obstruct the activities of the commission shall be punishable with rigorous imprisonment not less than two years and not exceeding ten years; with fine not less than Birr five thousand and not exceeding Birr twenty thousand. Where the offence is accompanied by violence the maximum penalty prescribed in this sub-Article shall be imposed.

7. Where the offences specified in sub-Articles 1,3,4,5 and 6 of this article are committed by juridical persons, the punishment with a fine shall be five fold.

24. Transitory Provision

1. Any corruption cases or other cases related with corruption which have been committed prior to the coming into force of this proclamation and the investigation of which have been just started, or undergoing, or finalized, or which have been in the process of trial, shall continue to be handled and decided in the same manner.

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ ከመቋቋሙ በፊት በተለያዩ አካላት ተይዞ እየታየ የነበረ ከባድ የሙስና ወንጀል ጉዳይ እንደአስፈላጊነቱ ለኮሚሽኑ ሊተላለፍ ይችላል።

3. ዝርዝሩ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

25. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል።

2. ኮሚሽኑ ይህንን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡትን ደንቦች ለማስፈጸም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

26. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጐች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ሕግ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

27. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህርዳር
ታህሳስ 5 ቀን 1996 ዓ/ም

ዮሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዚዳንት

2. Without prejudice to sub-Article 1 provided in this Article, a case of rigorous corruption offence, which was held by various bodies before the establishment of the Commission, may be transferred to the Commission as deemed necessary.

3. Particulars shall be determined by directive issued by the Commission.

25. Power to Issue Regulation and Directive

1. The Council of the Regional Government may issue Regulations necessary for the implementation of this proclamation.

2. The commission may issue directives necessary for the implementation of this proclamation and regulations to be issued pursuant to this proclamation.

26. Inapplicable Laws

Any law, which is inconsistent with this proclamation, shall not be applicable on matters covered in this proclamation.

27. Effective Date

This proclamation shall come into force as of its publication date in the zikre-Hig Gazetta of the Regional State.

Done at Bahir Dar,
This 15th day of December 2003.

Yosef Retta
President of the Amahra
National Region.